# ታላቅ የታሪክ ምፅት

ነጻነት ዘገዬ

ነሐሴ 28 ቀን 2004ዓ.ም(ሌሊት 11፡00 ሰዓት)

ይድረስ ለእውነተኛ ኢትዮጵያውያን

በያላችሁበት

መነሻ፡- ከዘመናት በፊት በእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ከፍተኛ ጦርነት ተካሂዶ ነበር፡፡ የዚህ ጦርነት ሰበብ ይህ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መንግሥት ጠቅላይ አዛዥም ሆነ ከመሠረቱ ፈጣሪው ራሱ ቅዱስና የጌቶች ጌታ የሆነው ***እግዚአብሔር*** እንደሆነ የምናምን እናምናለን፡፡ በዚህ መንግሥት ሥር እልፍ አእላፋት ወትልፊተ አእላፋት የሚሆኑ እንደሰማይ ከዋክብት ቁጥር ሥፍር የሌላቸው መላእክት ይገኛሉ፤ እነኚህ መላእክት እግዚአብሔርን በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ያገለግላሉ፡፡ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የቅርብ የበላይ አለቃቸው ሊቀ መላእክቱ ሣጥናኤል ነበረ፡፡ ይህ መልአክ አለቃ እንዲሆን የተመረጠውም በዕውቀቱና በሥነ ተፈጥሯዊ አቋሙ ከሌሎቹ በልጦ በመገኘቱ ነው፡፡ ይህ ብልጫው ታዲያ ውስጣዊ ትምክህትና ትዕቢት ስለፈጠረበት በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ መፈንቅለ መንግሥት እንዲያካሂድና ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠር ፍላጎት አደረበት፡፡

ከዕለታት በአንደኛዋ ይህን የዚያን መልአክ ክፉ ሃሳብ የተረዳው እግዚአብሔር ከመንበሩ ዙፋን ተነስቶ ለጊዜው ይሠወርባቸዋል፡፡ ይህን መሰሉን አጋጣሚ ይመኝ የነበረው ሣጥናኤል - ሰልቢያኖስ የሚለውን ጨምሮ አሁን በብዙ ስሙ የምንጠራው ሰይጣን - የፈጣሪውን ዙፋን ባዶ መሆን ሲረዳ ወዲያውኑ ሄዶ ይቀመጥበታል፤ እንዳማረበትና እንደሚስማማውም ራሱን ያሳምናል፡፡ ይህ ከሌሎቹ አገልጋይ መላእክት በተወሰኑ ነገሮች ብልጫን ያገኘው መልአክ የፈጣሪን ቦታ ተክቶ ፈጣሪ ነኝ ለማለት ምቹ አጋጣሚ ያገኛል፡፡

በብዙ ገጽታው ከእግዚአብሔር በመመሳሰሉ ምክንያት በፈጣሪ የችሎት ዙፋን ላይ ተቀምጦ ለታያቸው መልአክ ሌሎች የዋሃን መላእክት በስህተት እንዲሰግዱለት ከዚያን ጊዜ በፊት ያልነበረ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ፤ እሱም እጅግ በጣም ደስ አለው፡፡ አንዳንዶች ግ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ማን መሆኑ አደናግሯቸው - ቅ. ጳውሎስ በየምናውቀው ቋንቋ ስለቅዱስ አባት ኀያው እግዚአብሔር እንድንናገር ባሳሰበን መሠረት ከግዕዙ ይልቅ በሚገባ በማውቀው በአማርኛ ላድርገው - "ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የትአል? ማንስ ፈጠረን?" ብለው ሲጠይቁ ሣጥናኤል "እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ" ይላቸዋል፡፡ ሠራዊተ መላእክት በ‹ነው›ና ‹አይደለም› ለሁለት ይከፋፈላሉ፡፡ ጠንካሮቹ "ፈጣሪያችንን እስክናገኝ በጽናት በያለንበት ቆመን እንጠብቅ!" ብለው ሲከራከሩ ደካሞቹ "የለም፣ ፈጣሪያችን ይሄውና - ፊት ለፊታችን በዙፋኑ ላይ ያለው አይደለምን? ስለዚህ ለእርሱ እንገዛ፣ እንስገድለትም" ይላሉ፡፡ በዚህ የሃሳብ ክፍፍል የጦፈ ክርክርና ቀጥሎም የከረረ ጦርነት ይነሳል(በ93ዓ.ም. ብኤልዘቡሉ መለስ በአሸናፊነት የወጣበትን የወያኔ ‹ህንፍሽፍሽ› ያስቧል)፡፡ ያኔ ከፍተኛ ሥልጣን ያልነበራቸው እነቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል የነበሩበት የሣጥናኤል ተጻራሪ ቡድን ያን መፈንቅለ መንግሥት ለማክሸፍ ከፍተኛ ፍልሚያ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ነገር ግን የሰይጣንን ጎራ የሚቀላቀሉ ‹የዋሃን› መላእክት በመብዛታቸውና ሣጥናኤልም በማየሉ ወደሽንፈት ይቃረባሉ፡፡ ይሄኔም ሣጥናኤል ከነሠራዊቱ ክንፋቸውን እየነጨ ለሽንፈት ሊዳርጋቸው መቃረቡን የተገነዘቡት እነቅዱስ ሚካኤል ለጊዜው ወደተሠወረው እውነተኛው አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ይጸልያሉ፤ የጦርነቱም ድል ለእውነተኞቹ የእግዚአብሔር መንበር ቀናኢዎች ይዛወራል፡፡ ወዲያውኑም ፍርድ ይሰጣል፤ የዲያብሎስ መኖሪያም ይገለጣል፡፡ ሣጥናኤል ኃይለኛ ተከራካሪ በመሆኑ "ለስደትና ለመከራ ከጣፍከኝ ብቻየን እንዳልሆን እባክህን ባይሆን ከኔ ጋር ቆመው የተዋጉልኝን መላእክት የኔ ኃሻጓሬ እንዲሆኑ ፍቀድልኝ" ብሎ ፈጣሪን ይማጸናል፤ ይፈቀድለታልም፡፡ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ የሲዖል በሮች ተከፈቱ፤ ደምበኞችንም እንዲያስተናግዱ ዝግጁ ሆኑ - አሁንና ሰሞኑንም ድረስ፡፡ ...

ውድ ኢትዮጵያውያን!

ይህ ፍካሬ ነጻነት ነው፡፡ ፍካሬ ኢየሱስ እውን ሊሆን ዳር ዳር በሚልበት ወቅት የአንድ ምሥኪን ወገናችሁን ኢትዮጵያዊ ፍካሬ ብትሰሙ ምንም አይላችሁምና መላ ትኩረታችሁን ለጥቂት ደቂቃዎች እንድትሰጡኝ ክርስቲያኖቻችን በኃያሉ እግዚአብሔር ስም፣ ሙስሊሞችን በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ፣ በጣም አዛኝ በኾነው፣ የዓለማት ጌታ በኾነው፣ የፍርዱ ቀን ባለቤት በኾነው፣

በማይወልደውና በማይዋለደው አላህ ስም እማጠናችኋለሁ፡፡ “ሃይማኖት የግል ሀገር ግን የጋራ” በመሆናቸው በሀገር ጉዳይ ሁላችንም አንድ ነን፡፡ በሃይማኖት ጉዳይ ገብቶ ይህ ነው ያ ነው የሚል ሰው ሞኝ ነው፡፡ ፈራጁ ሌላ በመሆኑ የቄሣርን ለቄሣር የእግዜርንም ለእግዜር መተው ነው የሚመረጥ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በሃይማኖት ረገድ የጎላ ችግር የለብንም፡፡ ሙስሊምና ክርስቲያን እየተጋባና እየተዋለደ ነፍስያው ወደፈለገችው ሃይማኖት በገዛ ፈቃዱ ወይም ቢያንስ ‹ከነፍስህና ከሃይማኖትህ ምረጥ› ሳይባል በመጠነኛ ቤተሰባዊ ግፊት ከአንዱ ወደሌላው እየተሳበ በሰላም የኖረ ሕዝብ ነው፤ ወደፊትም ከዚህ በበለጠ በፍቅርና በመተሳሰብ የሚኖርበት ዘመን ይመጣል - ከተነሳ አይቀር ብዬ እንጂ - ይቅርታችሁን - ዋና ነገሬ ይህ አይደለም፡፡

ሰሞኑን በሀገራችን እያየን ያለነው ነገር ከታላላቅ የምድራችን የታሪክ ምፀቶች በዓይነቱ ወደር የማይገኝለት ነው፡፡ እውነት ከነአካቴው ጨርቋን ጠቅላላ ከሀገራችን የወጣችበት፣ ሀሰት ከነሙሉ ክብሯ የነገሠችበት፣ ውሸታሞችና ኅሊናቸውን ለርሣቸው የሸጡ ዜጎች ለማጥናኤል ከሃዲ ‹ንጉሥ› ባለሟልነታቸውን በግልጽ ያስመሰከሩበት፣ ይሉኝታና ባህላዊ ወግ ልማዶች የተደፈጠጡበት፣ ዘውገኝነት ፈጦ የወጣበት፣ ይሉኝታና ሀፍረት ተሟጠው ያለቁበት፣ ሆዳምነትና ልታይባይነት  የሠፈኑበት በጥቅሉ ለኢትዮጵያና ለሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ከባድ ሥራ የተደቀነበት አጋጣሚ ታዝበናል፡፡ ይህ መጥፎ አጋጣሚ ለምን ተከሰተ ብሎ መጨነቁ ዋጋ የለውም፤ በዚያ ላይ “ሟች ይዞ ይሞታል” የሚለውን ብሂል መዘንጋት የለብንም፡፡ ሁሉም ሊሆን የግድ ነውና፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሰው ሃይማኖታዊ ታሪክ እንደሚያስረዳው ፣ ቀጥሎም  እ.ኤ.አ የዛሬ 2012 ዓመታት ገደማ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተፈጠረው ክስተት በጉልኅ እንደሚገልጸው በዚህች ምድር እውነት ብዙም እንደማይደላት ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ እንደተወገረችና እንደተቀጠቀጠች መኖሯን ነው፡፡ ክርስቶስ ገና ብዙ መሥራት እየቻለ ገና በሦስት ዓመታት ገደማ አገልግሎት ብቻ እንዲወሰን ያደረገው በሀገራችን ገብቶ እያመሰን ያለው የዲያብሎስ መንጋ በሰው ልጆች አድሮ ነው፡፡ ያ ከጽድቅ ሥራ በስተቀር ምንም እንከን ያልነበረበት ንጹሕ ሰው በከሃዲዎች እንዲሰቀል ከመሰቀሉም በፊት እንዲገረፍ፣ ምራቅ እንዲተፋበት፣ የእሾ አክሊል ለፌዝና በፌዝ እንዲደፋበት… የተደረገው እውነት በዚህች ምድር ዋጋ እንደሌላት ለእኛም ጭምር ለማጠየቅ ነው፡፡ በሰሞኑ የኢትዮጵያ ታሪክም የተደገመው ያ ዓይነቱ የልበ ሥውራን ድርጊት ነው፡፡ በዚህ የዕብዶች የሚመስል ሰያጣናዊ ተውኔት ማን ይጠቀማል? እስከምን ያህል ጊዜ? ማንስ ይዋረዳል? ልምን ያህል ጊዜ? የሚሉት ቀላል ጥያቄዎች ናቸው አሁን በብዕር ያገናኙን - ለዚያውም ያሉን ውሱን የመገናኛ አውታሮችም ካልተጓደዱብኝ ነው ልንገናኝ የምንችለው፤ በኢትዮጵያዊነት ላይ ሸምቀቆዎች ይበልጥ እየጠባበቁ ስለሆነ ከመቻል ውጪ ለጊዜው ሌላ አማራጭ ጠፍቷል ወገኖቼ፡፡ ለአንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት  እርግጥ ነው እቅጩን መናገር ይከብድ ይሆናል - ምክንያቱም ለሰው ልጅ ያልተገለጠለት ብዙ ነገር አለና፡፡ ይሁንና ከሁኔታዎች በመነሳት በገደምዳሜ አካባቢያዊ ግምት መስጠት አያስቸግር ይሆናል፡፡ እመለስበታለሁ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ከ12ቱ ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስን በጣም ይወደው ነበር፡፡ ጴጥሮስ እንዲህ ይላል - “ጌታ ሆይ፣ እኔ እስከመጨረሻው አልክድህም፡፡” ክርስቶስም ይመልሳል፡- “እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ሌሊት ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ!” ክርስቶስ ያለው አልቀረም፡፡ ጴጥሮስ አውራ ዶሮ ሳይጮህ ለሦስት ጊዜያት ያህል “ይህን የምትሉትን ሰው እኔ አላውቀውም” ይላል፤ በሦስተኛውም የአውራ ዶሮው ጩኸት ላይ የጴጥሮስ ዐይኖች በጠላቶቹ ቁጥጥር ሥር ሆኖ የሞት ፍርዱን በስቅላት ይቀበል ዘንድ ይጠባበቅ ከነበረው ኢየሱስ ጋር ፊት ለፊት ይጋጫሉ፤ የገባው ቃል ትዝ ይለዋል፤ ቃሉን መብላቱም ይታወሰዋል፡፡ ወደ ውጪ ወጥቶም በፀፀት ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል፤ በዕንባውም ጥፋቱን ያጥባል…፡፡ የሚያለቅስ ኅሊና ያድለን፡፡ በቀዳሚነት ግን ከክህደት አባዜ እንዲያወጣን ፈጣሪን እንለምነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በከሃዲዎች ተጠርንፋ ተይዛለች፤ በትምህርት ላይ ናቸው ከሚባሉ ልደቱን ከመሰሉ የውርጃ ጭንጋፎች ጀምሮ በተቀናቃኝ ፖለቲካ መስመር እስከሚገኙ አስመሳይና ሥልጣን አሳዳጅ ዜጎች ድረስ ከሃዲዎች ሞልተውናል፡፡ ቤተ መንግሥቱማ የለየለት የከሃዲዎች ዋሻ ከሆነ ቆዬ፡፡ በእውነተኛ ኢትዮጵያውያን ምትክ የኤርትራ ተወላጆች ሥልጣኑን ተቆጣጥረው እያስረገዱን ናቸው፤ የገዳይና የጨፍጫፊያችንን ሬሣ ሳይቀር ከፍ ያለ ቦታ አስቀምጠው እንደጣዖት እየሰገድን እንድናመልከው በዓለም ፊት እያስገደዱንና እያዋረዱንም ናቸው፡፡ ለዚህ ሁሉ ግፍ ማጣፊያው ሲያጥራቸው የሚያይ የታደለ ነው፡፡ ወያኔዎች ማለት የማይነጋ መስሏት ወፍጮዋን ያበላሸችው ሴት ማለት ናቸው፡፡

መለስ ሞተ፡፡ ታዲያ ምን ይጠበስ? እኛ ገደልነው? ለአንዳንዶች ጥሩም ባይሆን - አምላካቸው የሞተ ያህል ቢቆጥሩና ቢያብዱ ቢሰክሩም - እሺ ይሁን የሞተው እንደተባለው የተፈጥሮ ሞት ነውና ሀገርን የሚያናጋ ክስተት በጭራሽ መፈጠር አልነበረበትም፡፡ ሀዘኑ የእውነትም ይሁን የማስመሰልና የጊዜ መግዣ ሁሉ ነገር ቀጥ ብሎ ለሁለት ሣምንትና ከዚያ ለሚያልፍ ጊዜ ይህን ያህል ብሔራዊ ሀዘን መታወጅ አልነበረበትም - ሊያውም ለይምሰልም ቢሆን የቆመው ሕግ ለአንድ ቀን ብቻ እየደነገገ፡፡ በማልቀስና ባለማልቀስ ተፈጥሯዊ የስሜት ኹነቶች ላይ ወያኔው ጣልቃ እየገባ ዜጎችን ትዝብት ውስጥ የሚያስገባ ዐውድ መፍጠርም አልነበረበትም - ምንም እንኳን አቋሙ እንደገበቴ ውኃ እሚዋልል የኅብረተሰብ ክፍል መኖሩን በአሳዛኝነቱ አምነን የምንቀበለው እውነት ቢሆንም፡፡ በሀዘን ምክንያት እጅግ ከፍተኛ የሀገር ሀብት በከንቱ መባከን አልነበረበትም፡፡ ብዙ የሥራ ጊዜ መጥፋት አልነበረበትም፡፡ መሆን ያልነበረባቸውን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ዘርዝረን አንጨርሳቸውም፡፡ በመሰል አጋጣሚዎች ሌላ ጊዜ መደገም የሌለባቸው በጣም ብዙ ስህተቶች ተሠርተዋል፡፡ በዓለም የሠለጠነ በሚባል ሕዝብ ዘንድም ለትዝብት ያጋልጠናል፡፡

በመሠረቱ ሰውዬው 57 ዓመት ኖሯል - ኖረ ከተባለ፡፡ ቀላል ዕድሜ አይደለም፡፡ አንዳንዶች ወደሕጻንነት ሁሉ ሊመልሱት (የሱዛን ራይስን የቀብር ዕለት ንግግር ያጤኗል) ቢከጅሉም 57 ዓመት ማለት በዘመኑ የዕድሜ ሥሌት ለ38 ዓመት ሕዝብን በዚህ ወያ በዚያ መንገድ ያገለገለ ሰው ይህን ያህል የሚያስለቅስ የልጅነት ዕድሜ አይደለም በምድር ያሳለፈው - እንደኪም ኢል ሱንግና እንደካሙዙ ባንዳ ወይም እንደሙጋቤ ዕድሜ ልኩን የሥልጣን ወንበር ላይ ተቀምጦ ካላመለከሁት ለሚል ሰው ካልሆነ በስተቀር ይህ ዕድሜ ቅልብጭ ያለና ከበቂ በላይም ነው፡፡ ይህ ሰው ከአፍሪካና በተለይም ከኢትዮጵያውያን አማካይ የዕድሜ ዘመን በአሥሮችና በሃያዎች አልፏል፡፡ 21 ዓመታትንም ኢትዮጵያን ቀጥቅጦና አንቀጥቅጦ ገዝቷል - ስንት እንዲጨመርለት ፈልገው እንደሆነ አይገባኝም፡፡ እነሱማ አበዱ እኮ! አብደውም አሳበዱን እንጂ፡፡ እንዴ! ከመለስ ሌላ ፈጣሪ መኖሩንም አንዳንዴ ይህን በመሰለው መጥፎ አጋጣሚ ይረዱ እንጂ፡፡ ሰው ይሙት መባል የሌለበት መሆኑን በበኩሌ የማምንበት መሆኔ በታሳቢነት ተይዞልኝ መለስ እንዲያ የአንድ እናቶችን ያንኑ ያላቸውን በአልሞ ተኳሽ እያስገደለ ሲያስለቅስ እንዳልኖረ ከአሥር የዜናዊ ልጆች አንደኛው ቢቀነስ ይህን ያህል ምድር ቃጤ መሆን ነበረባት? በደስታ ቤት አንዳንዴም ልቅሶ መኖሩን ይወቁት - ሞት ቤተ መንግሥት አይገባም የሚሉ ከሆነ ጅልነታቸውንም ይረዱ፤ ለዚያም ሳይሆን አይቀርም ሰምሃል መለስ ፈዝዛ የነበረችው - እንዴት ተደፈርን በሚል ስሜት ወይም ሁኔታውን ለማመን ባለመፈለግ፡፡ ለምን እኛ ብቻ ስናለቅስ እንኑር? ልቅሶና ሀዘንን ለእኛ ብቻ ደስታና ፈንጠዝያን እንዲሁም ያለምሕረት ግድያን ለነሱ ብቻ የሰጠ ማን ነው? እግዚአብሔር እንዲህ እንደሚጨክን ለወደፊቱ ይረዱት፡፡ ገልቱ ናቸው እንጂ ይህ ወርቃማ አጋጣሚ ብዙ ባስተማራቸው ነበር፡፡

የሟችን ኢትዮጵያዊነት ለታሪክ ፍርድ እንተወውና የገደሉት ግን ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑ ይገመታል - አባብሰውበት እንደሆነ ግን መጠርጠር ይቻላል፡፡ እንደሚመስለኝ ግን "በምርቃትም ይሁን በእርግማን እነሱ ገድለውታልና ባዶ እንዳደረጉን እኛም እናዋርዳቸዋለን፤ በዓለም ፊት እናቀላቸዋለን፤ የእስከዛሬውን ጥላቻቸውን በልዩ ድራማ ወደተለዬ ቅርጽ ለውጠን ቅሌት በቅሌት እናከናንባቸዋለን" ብለው ቆርጠው የተነሱ ይመስላል፡፡ የዚህ ሰውዬ ሞት በፈጠረው ልዩ አጋጣሚም ይሄውና መቼም የማያገኙትን ዕድል አግኝተው ዕድሜ እነኃይሌ ገ/ሥላሤንና ሠራዊት ፍቅሬን ለመሳሰሉ አጋሰስ ጌኛዎች ሊያዋርዱን ሞከሩ፤ አንክድም በሚገባ ተሳክቶላቸዋል፡፡ ግን ወዮ ለነዛ ለኢትዮጵያ አዋራጆች!!!! ከዋናዎቹ አዋራጆቻችን በበለጠ የሚገረፉት እነዚህ የተጋቦት ወያኔዎቹ ናቸው፡፡ ሠራዊት እንዲህ አለ አሉ፡-"ለጠ/ሚኒስትራችን ያለንን ፍቅር ለመግለጽ ኃይለኛ ዝናብና በረዶም ቢሆን ጥላና የዝናብ ልብስ እንዳትይዙ፤ አደራ!" ቀፎ ራስ! እነዚህን ይዘን ነው እንግዲህ የኢትዮጵያን ነጻነት የምናበሥረው? ቂናው ተሰፍቶ አልቋል! ግን አይዞን! ወላድ በድባብ ትሂድ፡፡ ጀግናና ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን አሉን፡፡ እሱ ሲል ከየበኣታቸው ይዘልቃሉ፡፡ ሰው ዝም ቢል እግዚአብሔር ዝም አይልም፤ ምድራችን የቃል ኪዳን ምድር ናት፡፡ ስለዚህ ተስፋችን በእግዚአብሔርም ነው፡፡

በዚሁ ቅኝት እመለስበታለሁ ወዳልኩት ልመለስ፡፡ የኢትዮጵያ የነጻነት ዕለት ከመቅረቡ የተነሣ በእጅ የሚጨብጡት ያህል በሚደረስ ቅርበት ላይ ይገኛል፡፡ እመኑኝ እጅግ እጅግ ቀርቧል፡፡ በሆድ ለማሰብ ዳር ዳር እያላችሁ ያላችሁ እንደዐይጧ እንዳትሆኑ ሀገራችሁን ከመክዳታችሁ በፊት ሁለት ጊዜ አስቡ - ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ሲቀር ሲጥ እንደሚባለው እንዳይሆን፡፡ እንደደገኞቹ መላእክት በያላችሁበት ጽኑ፡፡ እንጀራ አይፈትናችሁ - ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርምና፡፡ ለእንጀራ ብላችሁ ራሳችሁንና ትውልዳችሁን ለውርደት ከምትዳርጉ ያገኛችሁትን እየቀመሳችሁ ጤነኛ እግር ያላችሁ በእግራችሁም ቢሆን እየተጓዛችሁ አንገታችሁን ቀና አድርጋችሁ

የምትሄዱበትን የሁሉም የሚሆን ዘመን በትዕግስት ጠብቁ፡፡ ሁሉ ነገር አልቋል፡፡ የመከራ ደብዳቤያችን ጨርሶውን ሊቀደድ የቀረው በጣም ኢምንት ጊዜ ነው፡፡ በ"የዐይጥ ምሥክር ድንቢጥ" የኩሸት ዘይቤ የውስጣችንን የከሰለ አንጀት ሊያዩ የማይፈልጉ አላጋጮች በመለስ ሬሣ ላይ መለስን እየካቡና ‹ዕድገታችን›ን እያወደሱ በርሱ አመራር እንዳለፈላት ቢወተውቱም እውነቱ ባለበት ስላለ ዘመኑ ሲደርስ መለስና ጉግማንጉግ ግሪሣ ቡድኑ የጣሉብንን የታሪክ ጠባሳ ገልጠን እናሳያቸዋለን፤ ያኔ ሀፍረት የሚባል ነገር ፈጥሮባቸው ከሆነ በአሁኑ ንግግራቸው እንዲያፍሩ እናደርጋለን፡፡ ይህ ሁሉ ዝባዝንኬ የመጨረሻው መጀመሪያ እንደሆነ እንቁጠረውና የሀገር አድን ጥሪው የሚደርሰን ሰዎች ተገቢውን ምላሽ እንስጥ፡፡

የነጻነታችን መምጣት ለድርድር የሚቀርብ አይደለም፡፡ ደርሷል፡፡ ነገር ግን እርግማን አለብን፡፡ የኔም ሊጨመር ነው፡፡ እኔም እንዳቅሜ በሀገሬ ነገር ብዙ አይቻለሁ፤ ስደትን፣ ርሀብን፣ አእምሮአዊና ሥነ ልቦናዊ እንግልትን፣ የኑሮ ውድነትን፣ ውርደትን፣ ከጭንቀትና ጥበት የተነሣ እንቅልፍ ማጣትን፣ በግል  ሕይወት ምቾትን፣ ቤተሰብን በቅጡ አለመምራትን፣ ቋሚ ብስጭትን… እነዚህንና መሰል ኪሣራዎችን አስተናግጃለሁ፤ በግድ አካሌ መቆረጥ ወይም ደሜ መፍሰስ የለበትም፡፡ እንደብዙዎች ኢትዮጵያውያን ብዙ ተጎድቻለሁ፡፡ ስለዚህ ብራገም አደርሳለሁ፤ በዚያ ላይ የምላሴን ጥቁረት ብታዩት!

የኃይሉ ገ/ዮሐንስን(ገሞራው) ቃለ መጠይቅ በኢትኦጵ መጽሔት ሳነብ ሀገራችን ለስምንት ጊዜያት ያህል ተረግማለች ይላል፡፡ ለዝርዝሩ ጊዜ የለንም፡፡ እኔ በዘጠንኛነት ልገባ ነው፡፡ ኢትዮጵያችን ለጊዜው የከሃዲዎችና የሆዳሞች ምድር መሆኗ ካልቀረ እርግማን መጨመሯም አያስገርምም - ያበጠው ይፈንዳ፤ ካልደፈረሰ አይጠራም፡፡ እናም ይህን የሆዳምነት ወረርሽኝ ለማስወገድ በሀገራችን የድኝ እሳት ይዝነብ፤ ሀገሪቱን ከጠላቷ ጋር ተባብረው የሚያዋርዷትን መዠገሮችንም ጠራርጎ የሚያቃጥል፣ ዘርም እንዳይወጣላቸው ከሥራቸው መነጋግሎ የሚጥል የሄሊየም ዝናብ ከላይ ይዝነብ፡፡ አምላከ ኢትዮጵያ የሚሣነው ነገር የለምና ቤተ ክርስቲያንን በአጠቃላይም የአምልኮ ሥፍራዎችን ለጎጠኛው የወያኔ መንግሥት አገልጋይነት ያዋሉ፣ በዚያውም የተቀደሰውን ለውሾች አሣልፈው የሰጡ የሃይማኖት አልባሳትንና የተቀደሱ ሥፍራዎችን ለዓለማዊ ጥቅሞችና ለማይረባ ጎጠኛ ዓላማ የሸጡና የለወጡ ሁሉ ከዚህ ከሚዘንብ እሳት ባለዕጣዎች ይሁኑ፡፡  በሆዳቸው እያሰቡ ሀገሪቱን ለወደርየለሽ ውርደት የዳረጓትና ሀቀኛ ወገኖችን የሀፍረት ማቅ ያለበሱ አርቲስቶችም ይሁኑ ነጋዴዎች፣ ምሁራንም ይሁኑ ተማሪዎች፣ ወታደርም ይሁኑ ካህናትና ጳጳስት፣ ሽማግሎችም ይሁኑ ወጣቶች፣ አማራም ይሁኑ ትግሬዎች፣ ጉራጌም ይሁኑ ኦሮሞዎች፣ ሥራ ይራቸውም አይኑራቸው … ማንም ለዚህች የኢትዮጵያ ምድር ውርደት ከወያኔዎች ጋር የተባበረ ከሚመጣው የእሳት ጅራፍ አያምልጥ፤ ከወገነበት የጥፋት ሠራዊት ጋርም ወደማይቀርበት እንጦርጦስ ይውረድ፡፡ ፈጣሪ የለመኑትን አይነሳምና ለኢትዮጵያ ገዳይ ለመለስ ዜናዊ ከምር ያለቀሱ ዜጎች ከምር የሚያለቅሱበት ሌላ አጋጣሚ ይፈጠርላቸው - እነሱ ከርሣቸው ስለሞላ - እነሱ የተመኙት ስለተሣካ በሚሊዮኖች ሞትና ስደት፣ ስቃይና እንግልት አላግጠዋልና ፈጣሪ ለክፉዎች የመደበውን ደመወዛቸውን አይንፈጋቸው፤ ያዋረዷት ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያን የሚጠብቋት ቅዱሳን መላእክት በነዚህ በሰሞኑ የወያኔ ቅቤ አንጓች ዜጎች ላይ የገሃነም ስሑል ነበልባላዊ የእሳት ሠይፋቸውን ይምዘዙባቸው፡፡ ኢየሱስ በቅ. ወንጌል "የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፎ የሚሰጥ የወፍጮ መጅ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቁ ባሕር ቢወረወር ይሻለዋል" እንዳለ እነዚህ የሁለት ሀገር ጌቶች የሆኑ በአፍ ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ በተግባር ግን ከሀገሪቱ አፍራሾች ጋር ተርቲበኛ ሆነው በሕዝብ ደምና አጥንት የሚነግዱ ዜጎች የመጨረሻ ዕጣቸው ሞትና ስደት ይሁን፡፡ በነፕሮፌሰር አሥራትና በነአሰፋ ማሩ ደም የቀለዱ፣ ነእነ እስክንድር ነጋና አንዷለም አራጌ የእሥራት ሥቃይ ያላገጡ ዜጎች ጥቁር ውሻ ይውለዱ፤ እስከወዲያኛ ዘር አይውጣላቸው - ዘላለማዊ ምድባቸው ጥርስ ማፋጨትና በሲዖል ትል መበላት ይሁን፡፡ ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ወላፈን ያወጣ ቅዱስ እግዚአብሔር ይህችን ሀገር ከተደገሰላት የጠላት ሤራና የገዛ ዜጎቿ ሆዳምነት ከፈጠረው አድርባይነትና መሀል ሠፋሪነት ባፋጣኝ ነጻ ያውጣት፤ በጉጉት ለምንጠብቃቸው ለበጎዎቹ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎችም ያስረክባት፡፡ ቀኑ ቀርቧል፤ ለቀኑ ጸልዩ! …

ቤተ ክርስቲያን ትጸዳለች፡፡ አሰስ ገሰሷ ይራገፋል፡፡ መዥገሮቿና ትኋኖቿ በፈላ ውኃ ይቃጠላሉ፡፡ በመጨረሻም ትታደሳለች፤ አዲስ ሕይወትም ትላበሳለች፤ በአስመሳይ ቀበሮና ተኩላዎች ሳይሆን በትክክለኛዎቹ ክርስቶሳውያን መልካም እረኞች የጠፉ በጎቿንም ትመልሳለች፡፡ በዓለምና በክርስቶስ እየተመላለሱ ለሁለቱም ሳይሆኑ ሁለቱንም ያሳዘኑ አባቶችና የቤተ ክርስትያን ‹አገልጋዮች› ባልተገባ መንገድ ያሸቃበጡበትን ዋጋቸውን ያገኛሉ፡፡ ክርስቶስ "የአባቴን ቤት መሸጫና መለወጫ አደረጋችሁት" ብሎ ያኔ ብትንትናቸውን

እንዳወጣው አሁን ደግሞ ከዚያ በባሰ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን እያረከሱና እያወደሙ የሚገኙ ተሸራሚጭ የሁለት ዓለም ሰዎችን አይቀጡ ቅጣት የሚቀጣበት ዘመን ተቃርቧል፡፡ ባለቤቷ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰሞኑ የቤተ ክርስቲያን ውርደት ምን የሚሰማውና ምንስ ሊያደርግ የሚችል ይመስላችኋል? የሃይማኖት የለሾችን ጣዖት ወስደው በቤተ ክርስቲያን መቅበራቸው ሳያንስ ቤተ ክርስቲንን በጉልበት ደፍረው ከላይ እስከታች ስዕለ መለስን ማንጠፋቸውንና ኅያው እግዚአብሔርን ትተው ሟቹን መለስን ማምለካቸውን አስተውሉ! ይህ ድፍረት በተዳፋሪዎች ላይ የሚያስከትለውን የማይቀር መቅሰፍት ከሚተርፉ ወገኖች መካከል ከሆንን እናያለን፡፡ እርግጥ ነው እየመጣ ያለው ዕልቂት ሰውን በዘርና በሃይማኖት እየለዬ አይመርጥም፡፡ ማን ሊተርፍ እንደሚችል የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው፡፡ ከሚተርፉት ለመደመር ግን በምክር ደረጃ ማንኛውም ሰው ጥቂት ቃላትን ሊወረውር ይችል ይሆናል፡ የኔ ይኼው፡- እውነትን መያዝና እስከሞትም ቢሆን የእውነት ባሪያ ሆኖ መጽናት፣ በሁለት ቢላዎ አለመብላት፣ ሀገርንና ሕዝብን ሳይከዱ በጽናት ማገልገል፣ የሃይማኖትንና የፖለቲካን - የነፍስንና የሥጋን - መንገዶች ጠንቅቆ በማወቅ አንዱን ከአንዱ አለማዋሰብ፣ ነፍስንና ሥጋን ከሚያቆሽሹ መጥፎ ነገሮች መታቀብ፣ የፍቅርና የመተዛዘን ስብዕናን መላበስ፣ ከዘረኝነትና ከሃይማኖታዊ ጽንፈኝነት ተላቅቆ በሰብአዊ ርህራሄና በሰው ልጅነት ብቻ ተቀራርቦ መረዳዳት ፣ አምላክ ኢትዮጵያ የዚህችን ሀገር ጠላቶች የዶግ ዐመድ ማድረጉ ስለማይቀር በምንም ዓይነት መንገድ የሕዝብን ችግር ለነሱ የደስታና የሀብት ምንጭ ከሚያደርጉ ወገኖች ጋር ተጣልፎ አለመገኘት፣ ... ያቺን ቀን ለማለፍም ሆነ ባለማለፋችን ከሚገጥመን ዘላለማዊ ሞት ለመዳን ይረዳናል፡፡

በአሁኒቷ ቅጽበትና በነጻነት ዕለት መካከል ያለውን የጊዜ እርዝማኔ በትክክል መለካትና ማወቅ እንደማይቻል የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም እኔ አንድ ኃጥዕ የእግዚአብሔር ባሪያ  እንደ ዋልድባ አባቶቼ "ወይ ውረድ ወይ ፍረድ!" ብዬ የምጥለው የጽድቅ መቋሚያ ወይም ሳልደግመው በዕልባት ከድኜ እማስቀምጠው በናርዶስ የጸሎት ሽቶ የታወደ ክቡር ወንዑድ የጸሎት መጽሐፍ ባይኖረኝም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መቅሰፍቱን እስኪያወርድና የታሪክ አረሞችን ጥግ እስኪያሲዝ  ድረስ ከዛሬ ጀምሮ ***ብዕሬን እጥላለሁ***፡፡ እንዲህ የተቀለደባት ኢትዮጵያ አፈሯን አራግፋ እስክትነሣ ቀዳሚዋ ባንዲራም በአደባባይ እስክትውለበለብ ድረስ  እንደብዙኃን ወንድምና እህቶቼ እንዲሁም አባትና እናቶቼ በኅቡዕ ከመጸለይ በስተቀር ልፈንዳ እንጂ እንደ እስካሁኑ ጩኸቴን በወረቀት አላሰማም ፤ ሶማሊያና ፊጂ እንኳ ትናንት ተፈጥረው በኢንተርኔት ሲንበሸበሹ በዚች ታላቅ ሀገር ይሄ ትንሹ ነገር አንኳን የለንም፡፡ የለየለት እሥር ቤት ውስጥ መኖር ይሻላል - ሰውም ያዝንልሃል፡፡ እንዴ? ሣቅም በመንግሥት ልቅሶም በመንግሥት፡፡ አንተ ምንም የለህም፡፡ ስትስቅ አስፈቅደህ፣ ስታለቅስ አስፈቅደህ ይዘለቃል? አሁን አልቅስ፣ አሁን ሳቅ፣ አሁን ተኛ፣ አሁን ተነስ፣ አሁን አግባ፣ አሁን ፍታ፣ ... እየተባልክ አንቀልባ ውስጥ እንዳለ ሕጻን በመንግሥት ሞግዚትነት መኖር አይሰለችም? እንዲህ ዓይነት ኑሮ በለየለት የሲዖል ፍርድም ያለ አይመስለኝም፡፡ ሲያላውያን እሁድ ይሁን ዐርብ የሣምንት ዕረፍት አላቸው ይባላል፡፡ እኛ እኮ ካለ አንዳች ዕረፍት እነመለስና በረከት ጢባ ጢቤ ሲጫወቱብን ይሄውና 21 ዓመታችን አልፎ 22ኛው ከተጀመረ ቆዬ፡፡ ታዲያ ከአሁን በኋላ ነጻነት አይገባንም? ለዚህ ነጻነትስ የመለስ ሞት በቅድመ ሁኔታነት ቢታሰብ ምን ኃጢያት አለው? ምንም፡፡ የበከተው ቤተ አምልኮ እንዲጸዳ ጠረጋው ከራስጌው መጀመሩና ያንንም በይሁንታ መቀበሉ ምን ክፋት አለው? ምንም፡፡ የጽዳት ዘመቻ ሲጀመር ሆዳችን የባባውና ውስጣችን እየዘፈነ በውጫችን የምናነባው የጽዳቱን ዳር ድንበር አለማወቃችን ያመጣብን የንክኪነት ፍርሀት ይሆን? መጠርጠር ነው! ሁሉንም ጊዜ ባለውሉ ያሳየናል - ለሚያሳየን፡፡

ለማንኛውም ከወጀቡ የምትርፍ ከሆነ በምትተርፉ ጥቂቶች መሃል ይህን አሣፋሪ ዘመን እያነሳን እንጫወታለን፤ አሊያም ይህ ቀረብኝ የምለው ነገር ስለሌለኝ እንደፍጥርጥሩ - በቅድሚያ  ሀገር ሳይኖረኝ ‹ይህ ቀረኝ› የምለው ነገር ሊኖረኝ አይችልምና፡፡ ልጆቼና ልጆቻችን ጥሩ የወደፊት ዕድል ቢገጥማቸው ደስ ይለኛል፡፡  በነጻነት ማግሥት መገናኘት ለሚችሉ ግን መጥፎነቱ ያኔ ብዙ ሰው አይኖርም እንጂ ሙብል መጠጥስ እንደልብ ነው፤ እሾህ አሜከላውን ጎርፉ ስለሚጠራርገው ያኔ ፍስሐ ወሃሤት እንጂ ቁዘማና ልቅሶ አይኖሩም ...፡፡ ለማንኛውም የዚያ ሰው ይበለን፡፡ (ማሳሰቢያ፡- ትንቢታዊ ጥቆማዎች የኔ አይደሉም - ካነበብኩትና ከሰማሁት በራሴው ቋንቋ ያጠናቀርኩት ነው፤ ሊያውስ ምን ተናግሬ? እኔ ልቦናየ ያቀበለኝን የቆዩ ንግሮችን በዘወርዋራ ማስተጋባት እንጂ ከኔ ያልኩት ምንም የለም፡፡ ) ጣሊያን ሲሰናበት ‹አሪ ቬዴርቺ› ይላል፡፡ ‹በሰላም ያገናኘን› ለማለት፡፡(ነሐሴ 28 ቀን 2004 ከቀኑ 4:50 ሰዓት - አዲስ አበባ)